

**በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣**

**ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ**

# ከሴፕቴምበር 21-30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ

# እንዲሁም

# ከኦክቶበር 1-10/2025 እና ከኦክቶበር 11-20/2025

# የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ኦክቶበር 2025

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ


ባለፉት የሴፕቴምበር አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በመጀመሪያዎቹ ቀናቶች ላይ በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል አዲስ አበባ ቦሌ 32.4፣ አርባምንጭ 63.7፣ ባህር ዳር 41፣ ጎሬ 35.7፣ ነቀምት 67፣ አቦምሳ 35.2፣ አደዋ 34፣ አይራ 35.5፣ አማን 30.8፣ አንገር ጉጉን 32.4፣ አሶሳ 36፣ አዋሽ አርባ 30፣ ቡለን 34.2፣ 30.5፣ ቻግኒ 30፣ 31.6፣ 37.6፣ ጭራ 42.4፣ ዳንግላ 31.5፣ ጋምቤላ 30.7፣ ጋቲራ 31.7፣ ጊዳ አያና 32.9፣ ጊምቢ 55.1፣ ጂንካ 41.7፣ ካቺሴ 38፣ 56፣ ምዕራብ አባያ 39፣ ፓዌ 39.4፣ ሽሬ 33.7፣ ወራቤ 33.7፣ ባቱ 33፣ አቦ ሞሪንጋ 39.8፣ 45.2፣ አዲስ ዘመን 42፣ አዲ አርቃይ 30.1፣ 30፣ አለታ ወንዶ 30.8፣ አሮርሳ 32.2፣ ቢላም ቢሎ 39.6፣ 37፣ መንደር ሰባት 30.7፣ ዳራ ማሎ 30፣ 30፣ 30.2፣ ሃራ 30፣ 30.4፣ ቅዳሜ ገበያ 56.6፣ ኮበን 43፣ ቁሉቢ 57.7፣ ኩረፋ ጨሌ 31.5፣ ላንጌ 30፣ ሙጊ 33.1፣ ኦንጋ 33.7፣ 34.8፣ ዩና 36.5፣ ይርጋለም 36.5፣ መንደር 11 35፣ ሲቦ 42፣ እንዲሁም አዳሚ ቱሉ 32፣ 38.2 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል። በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ47 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብ፣ የደቡብ ምዕራብና የምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች፣ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት በደቡብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 39.6 - 67 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምት፣ አርባ ምንጭ፣ ቁሉቢ፣ ቅዳሜ ገበያ፣ ካቺሴ፣ ጊምቢ፣ አቦ ሞሪንጋ፣ ኮበን፣ ጭራ፣ አዲስ ዘመን፣ ሲቦ፣ ጂንካ፣ እና ባህር ዳር ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣


## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ




ምስል፡1 ከሴፕቴምበር 21-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን እና ምዕራብ ትግራይ ዞኖች፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋ፣ ጋሞ ወላይታ፣ጊዲዮ ና ባስኬቶ ዞኖች፣ ላይ ከ51-290 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ5-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡ በተጨማሪም የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ የዋግ ህምራ፣ የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ወሎ፤የመካከለኛዉና የደቡብ ምስራቅ ትግራይ ዞኖች፤ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ_ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ እና የሊበን ዞኖች፣አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ ከ11-50 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ2-6 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛና ምስራቅ ሸዋ ዞኖች፤ የምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ባሌ፣ የምስራቅ ሸዋ፣ ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ መካከለኛዉ፣ ምዕራብና ደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎና የደቡብ ወሎ እና የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የጎፋና ባስኬቶ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የቀልበቲ፣ ሃሪ፣ የጋቢ፣ ፋንቲ፣ አዉሲና ማሂ ዞኖች፣ ከሱማሌ ክልል የሲቲ፣ ፋፈን፣ ጃረር፣ የኤረር፣ ነጎብ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ እና የሊበን ዞኖች፣ አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ላይ በአብዛኛዉ መደበኛና ከመደበኛው በላይ  የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

Ethiopian Meteorology Institute

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባሳለፍነው አስር ቀናት በምዕራብ አጋማሽ፣ ደቡብ ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚገኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል እርጥበቱ በዚህ ወቅት ከምስራቅ እና ከሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ ቀስ በቀስ የሚቀንስበት ጊዜ ቢሆንም በምስራቅ እና አጎራባች በሆኑ የአፋር አካባቢዎች ላይ የተለያየ መጠን ያለው እርጥበት በማግኘታቸው ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበረ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት ደቡባዊ ክፍል እየተስፋፋ ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ እና ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንጻር በጎ ሚና ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 3/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የሴፕቴምበር ሶስተኛ አስር ቀናት በአባይ፣ በኦሞ ጊቤ፣ በባሮ አኮቦ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በአብዛኛው ተከዜ፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ፣ አዋሽ፣ በላይኛውና መካከለኛው ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሀ ፍሰት ነበራቸው። በተጨማሪም በጥቂት የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የመካከለኛው ዋቤ ሸበሌና ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች መጠነኛ የሆነ የገጸ ምድር የውሃ ፍሰት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበር። በአጠቃላይ ባለፉት ቀናት የነበረው የገጸ ምድርም ሆነ የከርሰ ምድር የውሃ ፍሰት የተሻለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ወደ ግድቦችና የተለያዩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የገባው የዉሃ መጠን ጨምሯል። ስለሆነም ለሀይል ማመንጫነትም ሆነ ለመስኖነት ለሚያገለግሉ ግድቦች የተሻለ የውሃ ግብዓት እንደነበረ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 5) ።





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


የበጋ ወቅት ከኦክቶበር እስከ ጃንዋሪ ያሉትን ወራት የሚያካትት ሲሆን፤ ለደቡብና ደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ነው፡፡ የበጋ ወቅት ከዓመታዊ የዝናብ መጠኑ እስከ 45% የሚደረሰውን የሚሸፍን ሲሆን ከበልግ ቀጥሎ የተሻለ ዝናብ የሚኖርበት ወቅት ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የዝናብ መጠን ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው በኦክቶበር እና በመጀመሪያዎቹ በኖቬምበር አስር ቀናት የሚጥለው ዝናብ ነው። በዚህ ወቅት ከፍተኛ መጠን ያለው የዝናብ መጠን የሚኖረው በደቡብ እና በደቡብ ምስራቅ አካባቢዎች ላይ ነው። በመደበኛ ሁኔታ በሀገሪቱ ደቡባዊ አጋማሽ ላይ የበጋ ወቅት ዝናብ ከኦክቶበር መጀመሪያዎቹ ቀናቶች ጀምሮ መዝነብ ይጀምራል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በመጪዎቹ የኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀኃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል (ካርታ 6 እና 7)፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኦክቶበር 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሡንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
| አሮሚያ | ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ቦረና ምስራቅ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | የፋፈን፣ ኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ዶሎ እና ቆራሂ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ጋሞ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| የክረምት ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ ዞኖች | | |
| አሮሚያ | የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| | ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| | የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | የአኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አፋር | የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ | መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ11 እስከ 29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ ሲቲ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በሚቀጥሉት የኦክቶበር ሁለተኛዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም የተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ ደቡብ ምስራቅ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምዕራብና ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅትን ዝናብ እያገኙ በነበሩት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ እንዲሁም በምስራቅ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ ፡፡

## 2.3 እ.አ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በምዕራብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው የክረምቱ ቀጣይነት ያለው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና፣ የሲዳማ ክልል ዞኖች፣ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚጀምረው የግብርና እንቅስቃሶ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| **የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች** | | | | |
| የቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ ትግራይ ዞኖች የካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች የአኙዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ የከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ እና ምዕራብ ኦሞ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የጥራጥሬ ሰብሎችን ለመዝራት<br>• ፍሬ በመሙላት ላይ ላሉ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሟላት | • የፀረ ሰብል ተባይ እና የአረም መከሰት | • የጥራጥሬ ሰብሎችን በጊዜ መዝራት<br>• የማሳ ክትትል ማድረግ<br>• ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር በተገቢ ቀንና ሰዓት መጠቀም<br>• አረምን ክትትል በማድረግ ማረም |
| **በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ምዕራብና ምስራቅ ሐረርጌ ዞኖች፣ አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ባሌ የዋግ ህምራ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የሰሜን እና ደቡብ ወሎ ዞኖች የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለመካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት<br>• ለቋሚ ተክሎችና ለግጦሽ ሳር ዕድገት<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | የፀረ ሰብል ተባይ እና የአረም መከሰት | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>• ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች ከሱማሌ የፋፈን ሲቲ እና ኤረር ዞኖች አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | | | ጋር በመመካከር መተግበር |
| የማሂ፣ ሀሪ፣ ቅልበቲ፣ ፈንቲ፣ ሀውሲ እና ጋቢ ዞኖች | ቀላል መጠን ያለዉ እርጥበት | • የእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት በመጠኑ መሻሻል | • የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም |
| **በጋ ሁለተኛ የዝናብ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች** | | | | |
| ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና ዞኖች የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ከሱማሌ ጀረር፣ ነጎብ፣ ዶሎ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ዳዋ፣ ሊበን፣ እና ቆራሂ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም<br>• ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል | • ከፍተኛ ትነት መኖር<br>• የአፈር ዉስጥ እርጥበት መጠነኛ መሆን | • የዝናብ ውሀን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል |

## 2.4 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በመጭው የኦክቶበር የመጀመሪያው አስር ቀናት በባሮ አኮቦ፣ የአባይ እና የኦሞ ጊቤ እንዲሁም የስምጥ ሸለቆ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ያገኛሉ፡፡ በጋ እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑት የዋቤ ሸበሌ፣ የኦጋዴንና ጥቂት የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት እንደሚኖራቸው ይጠበቃል፡፡ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የገጸ ምድር የውሃ ሽፋን | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ አብዛኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቢ ሸበሌ እና ኦጋዴንና ጥቂት ገናሌ ዳዋ | መካከለኛ | • የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች የውኃ መጠን ይጨምራል<br>• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይጨምራል<br>• የበመጠኑም ቢሆን ለከርሰ ምድር የውኃ ይዘትን ያሻሽላል<br>• የመጠጥ ውኃ አቅርቦት ሽፋን ይጨምራል | • በውሃ መያዣዎች ላይ የደለል ስጋት ሊኖር ይችላል | • የጎርፍ ተፅዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል |
| በአብዛኛው አባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ እና የታችኛው ገናሌ ዳዋ፣ እንዲሁም የዋቤ ሸበሌ ተፋሰሶች | መጠነኛ | • ግድቦች የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አይኖርም<br>• የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ይኖራል<br>• ለገጸ ምድር የውሃ ይዘት ጠቀሜታ ይኖረዋል | • ዝቅተኛ የውሀ ፍሰት መኖር<br>• እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት መከሰት<br>• ከፍተኛ ትነት መጨመር | • የሚገኘው መጠነኛ የዝናብ ውሃ ከጣራ እና ከመሬት ወለል በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ<br>• የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ የታችኛው ገናሌ ዳዋ እና ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም የአፋር ደናክልና አዋሽ ተፋሰሶች | ደረቅ | • የጎርፍ ስጋት አለመኖር | • የውሃ መያዣዎች የውሃ መጠን መቀነስ | • አልፎ አልፎ በሚኖር ዝናብ የጣራ ላይ ውሃን ማጠራቀምና ጥቅም ላይ ማዋል |